# ፖለቲካ እንደ ቧልት

## ነፋስ የሰረቀው ምርጫ

የቡድኑ አለቃ ጮሌ ጨልሌ ከተባለ ዓመታት ተቆጥረዋል:: መናገር ከጀመረ ቃላት ይነዱታል፤ የራሱን ድምፅ እያዳመጠ ይነጉዳል:: ጥጋብ ጥጋብ ካለው እነሆ ግንቦት 20 አስራ አራት ዓመት ሊያስቆጥር ነውና ሲናገር ስድብ ያበዛል:: ከተቀመጥክበት ወንበር ጋር ምላስህ አልሰምር አለ ሲሉትም የሚሰማ ሳይሆን ከተጫማለቅክ መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ ብሎ የሚደፍቅ በመሆኑ ደፍሮ የሚመክረውም ሰው ዛሬ የለም::

ጂሚ ካርተርም ብጤዎቹን ጭኖ፤ ቻይናውያንም ባገኙት ቀዳዳ ሊነግዱ ብለው፤ ትንሺቷ ርዋንዳ ደግሞ ከእኔም የባሰ አለ ለማለት የምርጫ ታዛቢዎች ሆነው ቢመጡም ወይም ቢልኩም የመለስ ዜናዊ ቡድን በአስገራሚ መንገድ ሽንፈት መከናነቡ አልቀረም:: ከቤተ መንግስት እስከ ባዕዳን መዲና ምን ተፈጠረ ወይም ከአሜሪካ መጤዎቹ እንደሚሉት ዋስአፕ! የሚለው ጩኸት ተበራክቶ መጥቷል:: ይህ ውለታ ቢስ ሕዝብ ቆይ ያገኛታል ብሎ መለስ ዜናዊ ዛተ ያሉ ክፍሎች ድሮም ትምክህተኞች ማድባትና ማጥቃት ያውቁበታል ሲሉም አማረዋል ተብሏል:: ሰዉ ሰልፍ ወጥቶ አቅዋሙን ግልፅ አድርጎ ነበር እኮ ላሉ ደግሞ የተሰጠው ምላሽ ለመዲናዋ እሺ በየባላገሩ ግን እንዲህ ማምረሩን ለምን ከመንግሰት ይደብቃል፡ የሚል ነው:: ለማንኛውም የአገዛዙ አፈ ቀላጤ በረከት ስምዖን ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ ምስጢሩን ሁሉ ገላልፆታል::

<u>በረከት ስምዖን/በስ/</u> -- ሕዝብ ከመንግሰት አቅዋሙን ደበቀ ማለት ፀረ ሰላምነት ነው::

ጠያቂ-- ሰሚ አጥቶና በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ ሆኖበት ሊሆን አይችልም?

በስ-- ከለፈለፈ ዋጋውን ያገኛል:: ነፃ ጋዜጣ እያሉ የሚያምሱን አይበቃም:: ሕዝብ ግን እንዲህ መሰሪ ሆኖ ማድባት አልነበረበትም::
ጠያቂ-- የሕዝብን የልብ ትርታ በተለይም የገጠሩን ሕዝብ ከእኛ በላይ የሚያውቀው የለም አላላችሁም ነበር?
በስ-- ብለናል::ሀቅም ነው:: ዛሬም ይደግፈናል::
ጠያቂ-- ታዲያ ለምን ለተቃዋሚዎች ድምፁን ሰጠ ?
በስ-- አወናብደውት ሊሆን ይችላል:: ግን ዋናው ተጠያቂ ነፋስ ነው::
ጠያቂ-- ነፋስ?
በስ--አዎ ነፋስ:: ለተቃዋሚዎች ድምፅ የሰጣቸው ነፋስ ነው:: ሰርተው ያገኙት ድምፅ አይደለም:: ነፋስ የሰጣቸው ነው::
ጠያቂ--ነፋስ ከተቃዋሚዎች ጋር ነው ማለት ነው?
በስ--አይገባህም እንዴ! ነፋስ እኮ የራሱን ዕድል በራሱ ወስኗል:: ያለፈው መንግስት ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር ሊያውል ተነስቶ አፈና አካሂዶ ነበር:: ድርቅና ነፋስ አምፀው ጥፋት ማድረሳቸውን ታውቃለህ:: የእኛ መንግስት ግን ለብሄረሰቦች የለገሰውን ለተፈጥሮም አልነፈገ:: የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው እንዲወስኑ ደነገገ ::ድርቅ ይኸው እስከ ከ14 ሚሊዮን ለመምታት ቻለ ::ኤይድስም ተስፋፋ:: በሽታም ተስፋፋ:: ነፋስም ባሻው ነፈሰ ::

ጠያቂ--ለምን ለእናንተ አልነፈሰም ታዲያ?
በስ-- ብዙ ምክንያቶች አሉት:: ግን ዋናው የነፋስና የንብ ጠብ ጋር ይያያዛል::
ጠያቂ-- አልገባኝም::
በስ--ቁስ አካላዊ ይዘቱን ትግል ሜዳ ሳለን ነው እኛ የተረዳነው:: ንብና ነፋስ ጠብ ናቸው:: የንብ ቀፎን ጠላት ጢስን የሚያናፍሰው ነፋስ ነው:: እኛ ደግሞ የምርጫ ምልዕክታችንን ንብ ስናደርግ ይህን አላሰብነም ነበር:: ለነገሩ አንዱ ተቃዋሚ የ ቪ ምልክት አድርጎ ነው ብቅ ያለው:: የፈረንጅ ቃል::ምን ማለት ነው?ኖንሴንስ! ሌላኛው ደግሞ ከእኛ በባሰ በቀላሉ ሊሳል የማይችለውን ፈረስ ነበር ያደረገው:: ትሮጃን ፈረስ?አታስቀኝ:: ውስጡ ያሉትን ድርጀቶችን እያወቅናቸው! ሕዝብ ማር ሰሪን ንብ ጠላሁ ሲል አላበደም ማለት አይቻልም::
ጠያቂ-- ለነፋስ መብቱን ከሰጣችሁት በኋላ ታዲያ ለምን ለእናንተ ብቻ አልነፈሰም?

በስ--እጃችን አመድ አፋሽ ሆኖ ሊሆን ይችላል። ይኸው ሕዝቡስ በል በነፃ ምረጥ ብንለው ወግዱ አላለንም። ይህ ምን ይባላል?
ጠያቂ--ምን ማድረግ አስባችኋል?
በስ-- ዓለምን ባስደነቀ መንገድ ተቃዋሚውን በማጭበርበር ከሰነዋል። በዓለም መንግስት እንዲህ ሲከስ የመጀመሪያው በመሆኑ ክብር አግኝተንበታል። ፌዴራል ፖሊስም ነፋስን በቁጥጥር አስገብቶ የትምክህተኞችና ጠባቦች እጅ ከጀርባው እንዳለ ያጣራል። እስከዚያው ደግሞ ነፋስ አላግባብ የወሰደውን ወደ ሳጥናችን እየመለስን ነው።
ጠያቂ--ማጭበርበር ቢባልስ?
በስ/በሳቅ/--እናስ? ምን ይጠበስ? ሕዝብ ሳናውቀው ጥላቻን አምቆና ስሜቱን ደብቆ መክረሙ ማጭበርበር አይደለም? አፀፋውን ነው የምንመልስለት። በስንት መቶ ሺ ለእኛ ሰልፍ ከወጣ በኋላ እስቲ አንተም ፍረደው ከመቸው የሰልፍ ወልፍ ይዞት ነው በእሁዱ ደግሞ ሚሊዮን ሆኖ የሚሰለፍብን!
ጠያቂ--የእናንተው ሰልፍ የግድ የተቃዋሚዎቹ ግን የውድ ነበር ነው የተባለው?
በስ-- ለእኛ የተሰለፈው ሰራተኛው ነው። ከስራ ገበታው በቀላሉ አይነሳም። የእነሱ ደግሞ ቦዘኔው ስለሆነ በየቀኑ ሰልፍ አይባልም እንጂ ሲዞር ሲንገላወድ ዋዩ ነው የመጣላቸው።
ጠያቂ-- እናንተ ስራ አሳጣችሁን እንጂ ቦዘኔ አይደለንም ነው የሚሉት።
በስ--ስራ አሳጣችሁን? ማነው ጦርነት ጭሮ ሳይከፍሉ ባድሜ ሽራሮ ያጓጓዛቸው? ወይ ጥጋብ! ወታደር ሁኑ አላልናቸውም። ሌላ ምን ይፈልጋሉ?
ጠያቂ-- ሰዉ ድላችንን ድምፃችንን ቀማችሁን ብሎ ቢያምፅስ?
በስ-- ይሞክረንና ያገኛታል!
ጠያቂ--ማንም በምርጫ አያሸንፈንም ስትሉ አይደል እንዴ ይኸው የተሸነፋችሁ?
በስ--ስንቴ ልንገርህ አንተ ሰው! ከነፃ ጋዜጠኞች ትውላለህ መሰል? ነፋስ ወስዶ ድምፅ ሰጣቸው ብዬ ነግሬሃለሁ። ያልሰሩበትን ያልለፉበትን የእኛ ማለት አይችሉም። በዝባዥ ስርዓትን የተዋጋነው ለዚህ ነው። ቁጭ ብለህ እንደ ፊውዳል መብላት አይቻልም። ከንብ መታረቅ ያቃተው ነፋስ አለና ድምፅ ሊወስዱ አይችሉም።
ጠያቂ--እነ ጂሚ ካርተርና አውሮጳውያኑም የነፋስን ሚና ተረዱ?
በስ--ጠቅላይ ሚኒስቴሩ እያስረዷቸው ነው። ከዚህ በፊት ነገሮችን እያሳመኗቸው ስለነበሩ የሚከብድ አይደለም። በተለይ ጂሚ ካርተር ይወዷቸዋል።
ጠያቂ--ተቃዋሚዎች ሕዝቡ እናንተን ጠልቶ ለእኛ ድምፁን ሰጠ የሚሉት ባዶ ነዋ?
በስ--ቀፎ፣ባዶ። ሕዝብ መንግስትን ይወዳል የሚለው ራሱ የፖለቲካ ሳይንስ ሀሁን ያልተረዱ የሚሉት ነው። ሕዝብ ጉምን አዘግኑኝ ይልና ቀን ስጠን ስትለው ያኮርፋል። ይህ የታወቀ ነው። አልገባህ ካለህ የዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት ያስረዱኃል። መንግስት ሕዝብን የመግራትና የማረቅም ኃላፊነት አለበት። መሪያችን ይህን የተረዱት ገና ደደቢት ሳሉ ነው። አይ ተመክሮ፣ አይ ችሎታ!
ጠያቂ--ሕዝብ በእናንተ ላይ ቅሬታ ነበረዋ?
በስ--በሰጠነው መብት ተጠቅሞ ቅሬታ ነበረው። ምን ያስገርማል? በአጉል ልወደድ ባይነት አልሰራንም እኛ።
ጠያቂ--ለእናንተ ድጋፍ ነፍጎ ለተቃዋሚዎች ከሰጠ አቅዋሙን አያሳይምን?
በስ--በምን ስሌት? ሚስትየዋ በባሏ ተቆጥታ በሩን ድርግም አድርጋ ብትዘጋው ከበሩ ጋር ነው ጠቧ?
ጠያቂ--የለም ከባሏ።
በስ--ኤክዛክትሊ። የሕዝብ አቅዋም ለተቃዋሚዎች ድጋፍን አያመለክትም። ለዚህ ነው ወዠንብር እንዳይኖር እርምት አድርገን ከልቡ ለእኛ ድምፅ መስጠቱን ለዓለም የምናሳውቀው።
ጠያቂ--ይገርማል። ወደ ነፋስ ልመለስና ከንብ ጥላቻ ሌላ ነፋስን ከተቃዋሚዎች ጋር ያቀራረበ ነገር ይኖራል ብለው ይገምታሉ?
በስ--እንዳልኩህ ጉዳዩ በምርምር እየተጣራ ነው። የፖለቲካ እስረኛ የለንም እንጂ ነፋስን በቀፈደድነው ነበር። የውጭ እጅ ያለበት ይመስለናል።
ጠያቂ-- ይህ ታላቅ ጉዳይ ነው። የእነማን እጅ?
በስ--ራሳቸውን ያውቃሉ። ያባረርናቸው ነበሩ። ሌሎችም ያሴሩብናል። ግን ሻዕቢያ አብሯቸው ነው።
ጠያቂ--ሻዕቢያ የተቃዋሚዎችን ማሸነፍ ይሰጋል፣ የእናንተን ድል ነው የሚመኘው ተብሏል...
በስ-- የቁርበትን ጉዳይ ለእኛ ተዉት ብሏል ጅብ። የሻዕቢያን ተንኮል እኛ እናውቀዋለን። ከዚያ ነው የመጡትና ወደዚያ እንመልሳቸው ያሉንም ኢንተርሃምዌዎችም ያውቁታል።

ጠያቂ-- ክሳችሁ መሰረት ቢኖረው ኖሮ ያ ሁሉ ተሰላፊ ወግዱ ሲላችሁ ምነዋ አንድ ህገ ወጥ ድርጊት አልተመዘገበ ?
በስ-- ከአሜሪካ ድረስ ያስመጣነው ጋዜጠኛ ቪዲዮ ካሜራ አልተዘረፈም? ይህ ምን ሊባል ነው? ትልቁንስ ነጋዴ ሌባ ብሎ መዝለፉ ወንጀል አይደለም?
ጠያቂ--ሰውየው ባዕድ ሆነው በሀገራችም ምርጫ ጣልቃ ገብተው የእናንት ደጋፊ
ስለሆኑ ነዋ?
በስ--ታዲያ ድጋፉን ዛሬ ጀመሩ? እስከዛሬ ምንው አልተወቀሱ፡፡ ጣልቃ መግባት ቢፈልጉ ኖሮ ባላቸው ገንዘብ ነፉስንም ይገዙልን አልነበረ ..
ጠያቂ--በራሳችሁ ከተማመናችሁ ለምን ሰልፍ ሁሉ ተከለከለ ?
በስ--አቤት ጉድ! 17 ዓመት ተከልከላቸሁ አልነበር?አሁን አንድ ወር ምን አላት? ያቀድነውን ከግብ ለማድረስ ሰልፍም ነፉስም አያስፈልገንም፡፡
ጠያቂ--እርሰዎስ በተመዘገቡበት ተሸነፉ የሚባለው?
በስ--የነፉስ ስራ፡፡
ጠያቂ--አቶ መለስ ለምን ታዲያ አልተሸነፉም?
በስ--በአድዋ የተቃዋሚዎች ሳጥን ስላልነበረ ነፉስ የት ወስዶ ይክተተው ብለህ ነው...
ጠያቂ--ተቃዋሚዎች በለስ የቀናቸው በነፉስ እንጂ በስራ አይደለም ብለዋል እርሶ.. እነሱ ግን ፕሮግራማችንን ሕዝብ ወዶልን ነው ባይ ናቸው?
በስ/እየሳቀ / -- የትኛውን? ያን ሁሉ ማን አንቦት ነው? ተወኝ እባክህ፡፡ ወይስ ለአዲስ አበባ የኤሌክተሪክ ባቡር እናስገባለን ያሉትን ወዶላቸው ነው?
ጠያቂ--ቢሆንስ?
በስ--ስማ የባቡሩ ዕቅድ የእኛ ነው፡፡ አርከበ ቤት ያፈርስ የነበረው ለዚሁ ቦታ መንገድ ለማግኘት ሲል ነበር፡፡ ሳታፈርስ ትገነባለህ? ባቡር በሰማይ ይሄዳል? የእኛ ዕቅድ የረቀቀ ስለሆነ ሕዝብ ሊገባው አልቻለም፡፡ቀለበት መንገድ ሰራንለት፡፡ሼራተን ቆመለት፡፡ ስንቱን ላንሳ...
ጠያቂ-- ሼራተን እናንተ  እንጂ ሕዝብ አይገባ?
በስ--በእኛ አደርጎ ሕዝቡ ይገባል፡፡ ወኪሎቹ እኮ ነን፡፡
ጠያቂ--መች መረጣችሁ?
በስ--ጠብቅ ድላችን ሲታወጅና ያኔ ማን እንደተመረጠ ታውቀዋለህ፡፡
ጠያቂ--ሕዝቡ የመረጠው ተቃዋሚዎችን..
በስ--የነፉስ ስራ...ነፉስ... ሁሉም ነፉስ፡፡ በኢትዮጵያ ብቻ ነው ምርጫ የሚሰርቅ፤ድምፅ የሚሰርቅ ነፉስ የተከሰተው ብለህ መዘገብ ትችላለህ፡፡ ሀቁ ይህ ነው፡፡